# እናስበው

የፍቅርን ሁሉ መጨረሻ
የመስዋእትነትን መዳረሻ
የግለኝነትን ማብቂያ
የትንቢት ቃሉን ማጽደቂያ . . .
አየነው . . . በመከራው በህመሙ
በስጋውና በደሙ . . .
በስቃይና በእንግልቱ
በስቅላቱና በሞቱ።
አየነው . . .
ከሰው ልጅ ሀጢአት ተሰዶ
ከአምላክነቱ ተዋርዶ
የስጋን መከራ ሲቀበል
ከእናቱ እይታ ሲነጠል።
አየነው . . .
እኛስ?
ከፍቅሩና ከመስዋእትነቱ
ከትኅትናውና ከትእግስቱ
በትንሹ ጨልፈናል?
ከጽናቱ ተምረናል?
ሌላው ቢቀር . . .
በዛሬው ቀን፥ በዚህች ሰዐት መከራውን አስበናል?
አልዋሽም. . .
አላሰብኩም።
ታድለዋል የሚያስቡ
ያምላክን ቃል አክብረው ትእዛዛቱን ያነገቡ
የጾም፥ የስግደት፥ የጸሎትን ክቡር ጻጋ የደረቡ
ለህማሙ ነቅተው ተግተው ደጀ ሰላም የሚውሉ፤
        ደጀ ሰላም የሚገቡ . . .
ታድለዋል።
እስቲ እኛም እንደነሱ
እንዳይርቅብን መንፈሱ
ላንዲት ደቂቃ እናስበው
ስለክብሩ እንዘክረው።
ምናልባትም . . . የትግላችን ፍሬ የዘገየው
ችላ ስላልነው ይሆናል . . . ከመሀላችን ስላራቅነው።
ኢትዮጵያ የአምላክዋ ናት የፈጣሪነቱ መመስገኛ
የፈሪሀ እግዚአብሔር ምንጭ የግማደ መስቀሉ መገኛ።
ስለሆነም . . . እናስበው
ምንጫችንን አናድርቀው።

---

ቴዎድሮስ አበበ
April 26, 2005